የሰበር መ/ቁ. 17712

ጥቅምት 16 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

**አመልካች፡** - የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት

**መልስ ሰጪ፡** - የወ/ሮ ሳድያ እስማኤል ወራሾች

*ስለባለሀብትነት ማስረጃ - የባለሀብትነት የርስት የምስክር ወረቀት - ተቃራኒ ማስረጃ - የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1195/1/፣ 1196/1*

መልስ ሰጪ በስር ፍ/ቤት በቀረበባቸው ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 5፣ ቀበሌ 09 የሚገኘውን የቤት ቁጥር 797 እና 798 የሆኑትን የንግድ ቤቶች ለስር ከሣሽ እንዲያስረክቡ ከተወሰነባቸው በኋላ አመልካች በክርክሩ ገብቶ ፍ/ቤቱ ውሣኔውን እንዲሽር ያቀረበውን ጥያቄ ንብረቶቹ ለመወረሳቸው ማስረጃ አልቀረበም በሚል ውድቅ በማድረጉና የተሰጠውንም ብይን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡



**ው ሣ ኔ፡** - የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያጸናው ብይን በአብላጫ ድምፅ ተሽሯል፡፡

1. የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል ለአንድ ሰው የተሰጠ የባለሀብትነትን የምስክር ወረቀት ማስረጃ የተሰጠው ሰው የዚሁ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡
2. ማስረጃው የተሰጠው ከደንብ ውጭ በሆነ አሰራር መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ከፍ/ብ/ህ/ቁ.1195 የተመለከተው የሕሊና ግምት ፈራሽ ይሆናል፡፡
3. በተሰረዘ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚገኝ የባለሀብትነት መብት አይኖርም፡፡

የሰበር መ/ቁ. 17712

ጥቅምት 16 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡ - የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ተስፋዬ ዘመድኩን ቀረበ

ተጠሪ፡ - የወ/ሮ ሳድያ እስማኤል ወራሾች እነ ወ/ሮ ሣባህ አብዶ/

ወራሽ አህመድ አብዶ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በሰበር ችሎቱ ለቀረበው ክስ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች በስር በመቃወም አመልካች በመሆን የሥር ፍ/ቤት ታህሣሥ 6 ቀን 1995 ዓ.ም. በዋለው ችሎት



በሰጠው ውሣኔ ላይ የተቃውሞ አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡ ይዘቱም ተቃውሞ በቀረበበት ፍርድ ተከሣሽ የሆኑት አቶ አማን መሐመድ ከመቃወም አመልካች በውል ተከራይተው የሚነግድበትን በወ.5 ቀበሌ 9 የቤት ቁ. 797 እና 798 የሆኑትን ንግድ ቤቶች ተቃውሞ በቀረበበት ፍርድ ከሣሽ የሆኑት ወ/ሮ ሳዲያ የግል ንብረቶች ናቸው በሚል ተከሣሽ ቤቶቹን ለቀው ለከሣሽ እንዲያስረክቡ እንዲሁም ከየካቲት 7 ቀን 1994 ጀምሮ ያለውን ኪራይ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ በመስጠቱ ነው፡፡ በመቃወም አመልካች ቤቶቹ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተወረሱ ላለፉት 28 አመታት ለአቶ አማን መሐመድ አከራይቶ ሲጠቀም መቆየቱንና ለከሣሽ ተሰጥቶ የነበረው ቁጥር 5127386 የሆነ የባለቤትነት ደብተር በአ/አበባ አስተዳደር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የቤቶች ጉዳይ መምሪያ የተሰረዘ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሮ የቆየ ቢሆንም ፍ/ቤቶቹ ስለ መወረሳቸው የሚያረጋግጥ የመረካከቢያ ቅጽ አልቀረበም በማለት የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ አድርጐታል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ በፌ/ከ/ፍ/ቤት ቀርቦ የነበረ ቢሆንም በተመሣሣይ ሁኔታ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

የአሁን አመልካች በሰበር አቤቱታው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በተሰረዘና ተቀባይነት በሌለው ማስረጃ ላይ ተንተርሶ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብሎ ያቀረበው ማመልከቻ የሕግ ትርጉም የሚያስነሳ ነጥብ ያለው መሆኑን በማመን ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ የተጠሪ መልስና የአመልካች የመልስ መልስ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ይህ የሰበር ችሎት ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ነጥብ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የተሰጠ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት በተሰረዘ ጊዜ ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚለው ነው፡፡

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1195 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በግልጽ እንደተመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባሀብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል ለአንድ ሰው የተሰጠ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ማስረጃ ለተሰጠው ሰው ለዚሁ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብት እንደሆነ እንደሚያስቆጥረው ተመልክቷል፡፡ በአንፃሩ ማስረጃው የተሰጠው ከደንብ ውጭ በሆነ አሰራር መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ከፍ ብሎ



በፍትሐብሔር ቁጥር 1195 ላይ የተመለከተው የሕሊና ግምት ፈራሽ እንደሚሆን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1196/1/ ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ በሕግ አግባብ ሥልጣን ተሰጥቶት ይህን መሰሉን የባለሀብትነት ማስረጃ የሚሰጠው ክፍል ቁጥር 5127386 የሆነውን የባለቤትነት ደብተር የሰረዘው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በተሰረዘ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት ደግሞ የሚገኝ የባለሀብትነት መብት አይኖርም፡፡ የተጠሪ ወራሾችም አውራሻቸው ያልነበራቸውን መብት ሊወርሱ አይችሉም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ከፍ ሲል በተጠቀሱት የሕግ ቁጥሮች መሠረት የባለሀብትነት የምስክረ ወረቀቱ የተሰረዘ መሆኑን የተረዳው ቢሆንም የባለቤትነት ደብተሩ መሰረዝ ለአሁኑ አመልካች የሚሰጠው መብት የለም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት ይህን ፍርድ በድምጽ ብልጫ ሰጥተዋል፡፡

**<u>ውሣኔ</u>**

- የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጥቅምት 10 ቀን 1997 ዓ.ም. በመ/ቁ. 15563 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

- ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**<u>የሐሳብ ልዩነት</u>**

በአንድ ክርክር ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም በክርክሩ ለመግባት የሚችል እና በክርክሩ ሳይካፈልበት የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማናቸውም ሰው ፍርዱ ከመፈፀሙ በፊት መቃወሚያ ሊያቀርብበት እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 ላይ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ አግባብ አንድ አመልካች ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በነበረው ክርክር ተካፋይ ሊደረግ ይገባው ነበር፤ አሊያም ሳይሟገትበት የተሰጠው ፍርድ የእርሱን መብት የሚጎዳ ሆኖ ተገኝቷል ይሰኝለት ዘንድ ለአብቱታው የአቀረበው ማስረጃ ይህንኑ የሚያረጋግጠለት እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በወረዳ 5 ቀበሌ 19 ውስጥ የሚገኙትን ቁጥር 797 እና 798 የሆኑ የንግድ ቤቶች የተጠሪዎች አውራሽ እንድትረከብ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ፍርድ መብቴን የሚጎዳው ነውና ገብቼ ተከራክሬ ፍርዱን እንዳሽር



ይፈቀድልኝ ሲል ይህን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 በመጥቀስ አቤቱታው ለተጠቀሰው ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ በቤቶቹ ላይ መብት አለኝ የሚለው ደግሞ በመንግሥት የተወረሱ ናቸው በሚል መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ይሁን እንጂ ቤቶቹ በመንግሥት የተወረሱ መሆናቸውን የማያሳይለት ማስረጃ አላቀረበም፡፡ የአቀረበው ሙግትም ይህ ማስረጃ አለኝ ወይም ነበረኝ በሚል አይነት ፍሬ ነገር ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡ በሌላም በኩል ንብረቱ ባለቤት የሌለው ጠፍ የሆነ ንብረት ነው የሚል ክርክርና ማስረጃ የሌለው በመሆኑ ጉዳዩ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1194 አግባብ ሊታይና የቤቶቹ ባለቤት መንግሥት ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ለተጠሪዎች አውራሽ ተሰጥቶ የነበረው የባለቤትነት ደብተር ተሰርዟል ማለቱ ብቻውንም ለእርሱ መብት የሚሰጠውና አቤቱታውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 አግባብ እንዲስተናገድለት ለማድረግ የሚያስችል አይደለም፡፡

በኔ እምነት የስር ፍርድ ቤቶች ወደ ዋናው ጉዳይ ተመልሰው ክርክሩን እንደገና መመርመር ሳያስፈልጋቸው አመልካቹን ወደ ክርክሩ ለመግባት የሚያስችልህ መብት መኖሩን አላስረዳህም በሚል ከወዲሁ

ጥያቄውን ውድቅ በማድረጋቸው የፈፀሙት የሕግ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም ውሣኔያቸው ሊፀና የሚገባው ነው በማለት ስሜ በሦስተኛ ተራ የተጠቀሰው ዳኛ አብዛኛው ድምጽ በተሰጠው ውሣኔ ባለመስማማት በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡



የሰበር መ/ቁ. 18307

ጥቅምት 25 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

5. አቶ አሰግድ ጋሻው

**አመልካች፡** - ንብ ትራንስፖርት አ.ማ

**መልስ ሰጪ፡** - አቶ ተገኑ መሸሻ

*የስራዎች አገልግሎት መስጠትን የሚመለከቱ ውሎች ለሰራተኛው ስለማገባው የደመወዝ መብት ስራ ላልተሰራባቸው ቀናት ደመወዝ ስላለማግኘት - ስለ ስራ አለመኖር /በድርጅት ውስጥ የስራ መሪ ስለሆነ ሰራተኛ/፡ - የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2534፣ 2540፣ 2541/1/*

መልስ ሰጪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በቴክኒክ ዋና ክፍል ኃላፊ ሆኜ ስሰራ ከስራ ከመሰናበቴ በፊት ታግጄ በቆየሁበት ከታህሣሥ 23 ቀን

1994 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሰኔ 5 ቀን 1995 ዓ.ም. ድረስ ያለው ደመወዜ እንዲከፈለኝ በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበውን ክስ ፍ/ቤቱ ተቀብሎ መ/ሰጪ የጠየቀው ገንዘብ እንዲከፈለው ውሣኔ በመስጠቱና ውሣኔውም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

**ውሣኔ፡** - የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያጸናው ውሣኔ ተሽሯል።

1. በድርጅት ሥራ መሪና በድርጅቱ መካከል ያለ የስራ ክርክር የሚዳኘው በፍትሐብሔር ህጉ የስራ አገልግሎትን መስጠት ስለማመለከቱ ውሎች ከቁጥር 2512 እና ተከታታዮቹ በተደነገጉት ህጎች መሠረት ነው።
2. የስራ መሪ ደመወዝ ለተሰራ ስራ ብቻ የሚከፈል እንጂ ላልተሰራ ስራ የሚከፈል አይደለም።
3. የስራ መሪው አንድም የስራ አገልግሎት ባይሰጥም እንኳን ይኸው ሁኔታ አሰሪው ስራ ሳይሰጠው በመቅረቱ ወይም እንዳይሰራ



በመከልከሉ የተነሳ እንደሆነ ደመወዙን ለማግኘት መብት የለው ውሉ ባልታገደበት ወይም ባልተቋረጠበት ጊዜ ሠራተኛው /የስራ መሪው/ ስራ ላይ ሆኖ ነገር ግን አሰሪው ሥራ ሳይሰጠው ወይም እንዳይሰራ በከለከለው ጊዜ እንጂ ሠራተኛው ከስራና ከደመወዝ ታግዶ የስራ አገልግሎት ላልሰጠባቸው ጊዜያት አይደለም።